አፍሪካ ቲቪ

1

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

# የአል ፋቲሃ ምዕራፍ

- በመካ የወረደች ስትሆን ምሉዕ ባርነትን ለአላህ ብቻ በማድረግ የአላህን ብቸኝነት ማረጋገጥ የሚለው ዋናው የምዕራፉ ዓላማ ነው።
- የተከበረው የአላህ መጽሐፍ ቁርኣን በዚህ አጭር እና ውብ ምዕራፍ ስለሚጀምር <<ሡረቱ አል-ፋቲሓ>> የመከፈቻይቱ ምዕራፍ በሚል ተሰይሟል።
- ከይዘት አንፃር በቁርኣን ሙሉ ምዕራፎች በዝርዝር የተዳሰሱ የአላህን አምላክነት አምኖ ስለመቀበልና እርሱን በብቸኝነት ስለማምለክ (ተውሂድ)፣ ስለአምልኮት፣ ስለታሪክ ጥቆማዎች እና ሌሎች አጀንዳዎችን ጠቅለል ባለ መልኩ ያቀፈ በመሆኑ <<ኡመል-ቁርኣን>> በመባልም ተሰይሟል።
- ፋቲሓህ ከቁርኣን ምዕራፎች ሁሉ የላቀ ምዕራፍ ነው።
  - <<አስ-ሰብዑል-መሳኒ>> የሚሰኝ ተጨማሪ መጠሪያም አለው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

( بسم الله الرحمن الرحيم)

- በአላህ በመታገዝና ስሙን በማውሳት ረድኤትን በመፈለግ በአላህ ስም ቁርኣንን ማንበብ እጀምራለሁ። <<በስመላ>> (ቢስሚላሂ አር-ራሕማኒ አር-ረሒም) የሚለው ሐረግ ከአላህ ውብ ስሞች መካከል ሦስቱን አካትቶ ይዟል።
- እነሱም:-

1. <<አላህ>>:- በእውነት ተመላኪ የሆነ ማለት ነው። ለአላህ ብቻ የሆነ ልዩ መጠሪያ ስም ነው። በዚህ ስም እርሱ ብቻ እንጂ ሌላ አካል አይጠራበትም።
2. <<አር-ራሕማን>>:- ትርጓሜው የሰፊ ምህረት ባለቤት ማለት ነው። እርሱ አላህ በራሱ እጅግ ርኅሩህ ነው።
3. <<አር-ረሒም>>:- ተደራሽነት ያለው እዝነት ባለቤት ማለት ነው። እርሱ በእዝነቱ ከፍጡራኑ ለፈቀደው ያዝናል። ከሰዎች መካከል አማኞች በዚህ (እዝነት) ውስጥ ይካተታሉ።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

(الحمد لله رب العالمين)

- አላህ የሁሉም ነገር ጌታ፣ ፈጣሪና አስተናባሪ (ተቆጣጣሪ) በመሆኑ፣ የልቅና እና የምሉዕነት መገለጫ የሆኑ ምስጉን ባህሪያት ሁሉ ለሌላ ሳይሆን ለርሱ (ለአላህ) ብቻ የተገቡ ናቸው።
- <<ዓለሚን>> ማለት <<ዓለም>> የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ስያሜ ሲሆን ከአላህ ውጭ የሚገኙ ነገሮችን ሁሉ ያካትታል።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

{ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ}

- በቀደመው አንቀፅ ከቀረበው ምስጋና በመቀጠል ለአላህ የቀረበ ተጨማሪ ውዳሴ ነው።
- እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ

1

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ
(ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ፋሓ")

አፍሪካ አካዳሚ

(مالك يوم الدين)

- በትንሳኤው ዕለት ለሁሉም ነገር ባለቤት መሆኑን በመግለፅ አላህን ማላቅ ነው።
- በዚያን ዕለት ማንኛውም ነፍስ ለሌላኛዋ ነፍስ አንዳችም ነገር ማድረግ አትችልም።
- <<የውመዲን>> ማለት የምርመራ እና ምንዳ ዕለት ማለት ነው።

1